# <u>በዳላስ ቴክሳስ የኢትዮጵያውያን ቀጣይ ፈተና</u>

የወያኔ ቀን እያጠረ ሲሄድ የእበላ ባይ ተስፈኞች እና በቀል ተሸክመው አገርን ለመጉዳት ወደሁአላ ያላሉት ሁሉን ጠል ሁሉን ተቃዋሚ አስመሳይ ዜጎች የምትጠልቀውን ጀንበር ማንጋደዱአን አለማወቅ ወይም ማኖ ከነኩ በሁላ የተሻለ አይመጣም (ለነርሱ ከርስ) በማለት በተቃዋሚው ላይ ላለፉት 18 አመታት የማክቸልቸል ዘመቻቸውን የበለጠ አጠናክረውና አቀናጅተው ለፈተና ዳርገውናል ለምላቸው አድር ባይ ቅቤ አንጉአቾች እንድንነቃባቸው ሰው አውቆ መስመር እንዲያስለያቸው ይህችን አጭር ማመልከቻ ጽሁፍ አቀርባለሁ።

እዚህ ባለንበት ከተማ ዳላስ ወያኔና የወያኔ ደጋፊወች አንድ ምናልባትም የመጀመሪያ በግልጽ የወጣ የኢሕአዴግ ድጋፍ ሰጭ ኮሚቴ በዳላስ ፎረትወርዝ (Ethio-American consensuses committee Dallas Fort worth) በሚል ተመስርቶ እየተንቀሳቀሱ መሆኑን በአይናችን አይተናል በጆሮአችን ሰምተናል። አንድ "ትኩረት" የተባለች በራሪ ወረቀት የከተማችንን ጉድ እና ምን እየተሰራ እንደሆነ ጠቁማናለች። በእውነትም አተኩሮ ለተመለከተ የወያኔና ደጋፊወቹ ዘመቻ እንዲህ አጣጥለን የምናየው አለመሆኑን ተረድተናል። ወያኔወች መልክና አይነታቸውን አነጋገርና አረማመዳቸውን ቀይረው በአለንበት ከተማ መንቀሳቀስ ከጀመሩ ቆይተዋል ግን እኛ ፈጥነን አለመረዳታችን ለጉዳት ዳርጎናል። ዛሬ በኮሚውኒቲ ስብሰባ ወይም በእድርና እቁብ ወይም በሐዘንና በደስታ ቦታወች የተሰማሩት የምናውቃቸው የጥንት የጠዋቶቹ የወያኔ ካድሬወች ሳይሆኑ እኛን ሆነው እኛን መስለው ስናዝን አዝነው ስንደሰት አብረው ቦርቀው ወይም የኛን ቃል ተናግረው ተቆርቋሪና አዛኝ ሆነው የኖሩት ከጥይት የቀደሙ በቀላሉ የማይበገሩ የጠላት አንባሳደሮች ከልክ በላይ ሆነዋል። ላስተዋለ መለያቸው ሥስና ቀላል ቢሆንም በመልካም ውይይት የምንለውን እያሉ ግን የጨዋታ ሜዳቸው በተቃዋሚው ወይም ወያኔን በሚአወግዘው ሜዳ እንዲሆን የሚነሱ ግልብ ውይይቶችም ሆነ የታቀዱ ወይም እንዲሁ ለሳቅ ለጨዋታ የታለሙትን ሳይቀር አነጣጥረው በኢትዮጵያ ተቃዋሚ ጎራ እንዲሸከረከሩ የሚያደርጉ መሰሪወችን ነው። የውይይት መነሻቸው ወይም የሳቅ የፈገግታ መጀመሪያቸው በማጣጣል በማናናቅ ላይ ያተኮረ ልክ የወያኔው ጠቅላይ ሚኒስቴር ያደርግ እንደነበረው ማለት ነው። "መንገዱን ጨርቅ ያድርግላቸው" "ግማሽ መንገድ ሄደን እንቀበላቸዋለን" አይነቱን አጣጣይ ፌዝ አዘል ግን ቅስም ሰባሪና በንቃት ላላስተዋለ በሾኬ መች ዘመቻ አንዱ ነው ለምሳሌ የውጭ ተቃዋሚ ስለአገር ቤቱ ምን ያውቃል? ከሞቀ ቤት እየኖሩ መረበሽአችሁን አቁሙ አይነቶች። ሌላው የወያኔ በስልጣን መቆየትም ሆነ ወደስልጣን መምጣት ያለምክንያት እንዳልሆነ የዚህ ድርጅት መሪወችን (እነ ስብሐት፤ መለስን ማለት ነው) እየሰደቡም እንኩአን ቢሆን ጠንካሮችና ጠበብቶች አርገው ያቀርቡልናል። ከሁሉም የሚገርመው ተቃዋሚወችን ማጣጣል ምርጫ 97 እንደምሳሌ ይወስዱና ተመልከቱ ህዝብ ያገኘውን ድል ተቃዋሚወች ባለመስማማት በመሻኮት እንጅ መንግስት (ወያኔ ማለት ነው) ምንም ያጠፋው የለም ይሉናል። ተቃዋሚወች 40 አመት ምን ለውጥ አሳዩ? ወይም ላለፉት 18 አመታት እርስ በእርስ ከመሻኮት ውጭ መቸ ተስማምተው ያውቃሉ ይሉናል። <u>የምርጫ 97ን ድል እና የሕብረት እና የቅንጅትን መልካም ስራወች ሊያስታውሱ አይፈልጉም</u>። ይህ መሰሪ ስልት በስራ መዋሉ ዛሬ አገር ገብቶ ያለሰቀቀን መውጣት የሚፈልገውን (ሆዳም) የሚባለውን አይነት ማለት ነው፤ የሌለ አፍ እንዲያገኝ፡ የሌለ ልቦና እንዲገዛ እረድቶታል ማለት ይቻላል።

ነፍስ ይማርና ወያኔን ገና ሚኒሊክ ቤተመንግስት ሳይገባ የደደቢት አልቤኒያን ኮሚኒስት እያለ ማለት ነው፤ ለምእራብ መንግስታት በተለየም ለአሜሪካና ለእንግሊዝ ቋሚ ወዶገባ አንባሳደር ነበሩ አስተዋወቁት የሚባሉት ዶክተር/ደጃዝማች እና አሁን በህይወት ያሉት አባ ጳውሎስ ያኔ በትግላቸው ዘመን ( የሚኒሊክን ቤተመንግስት ለመረከብ ያደርጉ በነበረው እሩጫ ጊዜ) እነኝህ ግለሰቦች ከሺህ አንባሳደሮች በላይ ስራ የሰሩት አንዱ በሐይማኖት አሳበው እና መስቀል ተሸክመው ሌላው የተከበሩ ሊቅና አዋቂ ብሎም አንድ ያገሪቱ ልኡል በመሆን ነበር። ታዲያ ያኔ ጉግ ማንጉግ ያሉትን መንግስት ማሳጣትና እነዚህን እውነተኛ ጉግ ማንጉጎች የተሻሉ አድርጎ ማቅረብ ዋና ስራቸው ነበር። በእውነቱም ተሳካላቸው። ሰኞና ሰኔ ገጥመው ያሰቡት ተሳክቶ ያባ ጳውሎስና  የዶክተር/ደጃዝማቹ ልጆች በለስ ቅንቶአቸው መንበረ ስልጣኑን ሲቆናጠጡ በሁሉም ልቦና (በእነሱ ማለት ነው) ለመቶ ምናምን አመታት ሲንከባለል የኖረው የበቀል እሳት አገሪቱን የባህር በር በማሳጣት ወይም ከጉሮሮዋ በላይ በመቁረጥ አላቆመም ያኔ እነዚያ ሁለት ሰወች ያገር እና የሐይማኖት ተቆርቋሪ መስለው በየከተማው እይተጋበዙ ይሰብኩ እንደነበር ትዝ ይለኛል። እዚህ ከምኖርበት ከተማም የአባ ጳውሎስን መቁጠር ባልችልም የተከበሩት ጨዋን ግን መጎኝዣ ከፍለው ያስመጡአቸው ወገኖች መኖራቸውን አስታውሳለሁ። በስብሰባው ቦታም ተገኝቸ አዳምጫለሁ። አንዳንዶች መሬት ዝቅ ብለው ሲስሙላቸው አይቻለሁ። ታዲያ ወያኔ ስልጣን በያዘ ማግስት ዋና አጋፋሪ መሆናቸውን ሳስታውስ አሁንም ይገርመኛል። የተከበሩትም ሆነ ጳውሎስ አገር ሲታመስና ሲቆረስ ተቃውሞ አላሰሙም። አዲሶቹ አስመሳዮች በተመሳሳይ ፈሊጥ ልባችንን ያወልቁታል። ይሁነኝ ብለው እራሳቸውን ጠልተው እኛም እኛነታችንን አክ ብለን እንድንተፋ ባዲስ መልክ የካድሬ ስራ ይሰሩብናል ።ያለፈውን አሳልፈን ጊዜ

እስኪያልፍ ብለን የደነዘዝን ብንመስልም ቀን ሲለወጥ ግን ያ አለም ያረገደለት 300 ሽህ ጦር እንደተፈታ የአናሳወቹም የረፋድ ጉም እንደሚሆን አንጠራጠርም። ልብ አውልቆች ዘረኛው ወያኔ እንደተለወጠ ሊሰብኩን ይሞክራሉ። ዳሩ ግን ዛሬም ከ 18 አመታት በሁዋላ አጥፊ ጸረ ኢትዮጵያ ባህሪው ቀጥሎ የነጻነት እና የኢትዮጵያዊነት ምልክት የሆነችውን፤ የደም ፍሳች ያጥንት ክስካሽ እና አያሌ ከዘመን ዘመን ባላቓረጠ መራር ገድል የቆመች ሰንድቅ አላማ እስካሁን ያብጠለጥሉአታል። የሌላትን ያልነበራትን ወይም ትውልዶች ያማያውቁላትን ቀለማት ይጨምሩባታል። ወይም እንደብጣሽ ጨርቅ ያረጉአታል። አለያም ያነጥፉአታል። አገሪቱም እንዲሁ ከገደል አፋፍ በቀጭን ገመድ ተደግፋ ቀኑአን እንደምትቆጥር መከረኛ በ አንቀጽ 39 ታጅላ ቀን ይቆጠርላታል። ወደተምሳሌየ ልመለስና እነዚያ ሁለቱ ሰወች አንዱ የሉም ሌላው ግን ዛሬም የሐይማኖታችንን መንበረ ስልጣን ተረክበው የተመረጡትን አባት አሰድደው ፈጣሪን አምነው ሳይሆን የግል ጠባቂ ጠበንጃ የታጠቀ ማለት ነው አስከትለው የመከፋፈል፤ የማዳከም፤ የእርቅንና የደግነትን ጎዳና ሳይሆን የበቀልን እና የክፋትን ተከትለው አጥፍተው ለመጥፋት ቁርጠኛ መሆናቸውን ቀን ከሌት ለልጆቻቸው (ለወያኔወቹ) ያስተምራሉ የወያኔውን መንግስት ስራ ይሰራሉ። አዲስ ምልምሎችን ያቀርባሉ። መሬትና ቤት ያሸልማሉ ምኑ ቅጡ። በምእራብ የሚከፈቱ አቢያተ ክርስቲያናትን አይታችሁ አስተውላችሁ ከሆነ በእሳቸው ተባርከው የተከፈቱት ሁሉ ዘርን ተንተርሰው የነእከሌ ነን ብለው እንደሆነ መረዳት አያቅትም። እዚህ ዳላስ አንድ ቢተክርስቲያን ከፈቱና የሁለት ታቦት ስም ሰጡት አለኝ አንድ ወዳጀ እኔ እንኩአን ብዙም አላዘወትርምና አላስተዋልሁም ነበር ታዲያ ማን አሉት ስለው። አይ አንተ በጳውሎስ የሚከፈት ምን ደግ ታስቦለት ብለህ በቅዱሳኑም መነገድ እኮ ከጀመሩ ቆይተዋል። እንሱን ይጠቅማል ያሉትን ሁሉ ከልክ ያለፈ የሞራል ብካች እንኩአን ቢሆን ለማድረግ ወደሁአላ አይሉም ታዲያ ይህ አዲስ የከፈቱትን የቅዱሳን ቤት መሆን የሚገባውን በመሰሪ ባህሪ አጅለው የሁለት ታቦት ስም ሰጡት ተክልየን እና አቡነ አረጋዊን አመጣን ብለው ከፈቱት አለኝ። ነገሩ አልገባኝም እና ፈርጠም ብየ እንዳወቅሁ ሆኘ አለፍኩት። እየቆየ ሲገለጥልኝ ያ ወዳጀ ተቆርቁሮ ሲያጫውተኝ የነበረው ጉዳይ ድንገት ብልጭ አለብኝ እና በእጅጉ ተገረምሁ። ይህም አለ ለካ እነዚህ ሰወች ክፋት ሲያስቡ ነው የሚያድሩት ማለት ነው ብየ ተገረምሁ። በእውነትም የመሐል አገር ደጋግ አማኒያን ተክልየን ለመሳለም ጳውሎስ ወድሚወደስበት የቆየውን እና ምእመናኑ የሰሩትን ለማዳከም ወይም ለመከፋፈል ታስቦ ለተዘየደው መሔዳቸው አልቀረም ማለት ነው። አቡነአረጋዊንም እንዲሁ። ታዲያ እነዚህ ሰወች በሐይማኖቱም ሆነ በማንኛውም ቦታና ጊዜ የሚሰሩት የዚህን ዘረኛ መንግስት እድሜ ለማቆየት ነው። ያ ሲሆን እንቃወማለን የሚሉትን ያለርህራሄ ስም ማጥፋት ዋነኛ ተግባራቸው ሆኑአል። ከላይ ከመነሻየ እንዳልሁት እና እኔንም ነጋ ጠባ አሁን ከሆነ ከሚገጥመኝ አድዱ challenge ወያኔ አትበሉአቸው ስማቸው ኢሕአዴጎች ነው። ጠላት አትበሉአቸው ወገኖች ናቸው። የጎዳን መንግስት ሳይሆን የተቃዋሚ አክራሪነት ነው በማለት ያሳጡናል። ታዲያ ለኔ ብጤ ደጋጉ እውነትም ይልና ተጨምሮ እራሱን ያከቸለችላል ማለት ነው።

ይህችን አጭር ጽሁፍ እንዳቀርብ ያደረገኝ ዋና ጉዳይ ወያኔና በሱ የድርጅት መዋቅር ስር ተሰልፈው፤ አላማየ ብለው ሌት ከቀን ደፋ ቀና ብለው ስለሚታገሉትና ስለታገሉት ሰው እንዲያውቃቸው ብየ አይደለም። የልቅስ እነሱ ገና ከጠዋቱ የዘረኝነት ጥንሥስ ሲቦቀር ጀምረው አምነውና ጸንተው ኢትዮጵያዊነትንና ኢትዮጵያውያንን ታግለዋል።፡አይሆንም ይላሉ ብለው የገመቱአቸውን ጠንካራ ዜጎች ገና ከጠዋቱ ጀምረው መንጥረዋል፤ ባደባባይ አርደዋል፤ በጥይት ደብድበዋል ወይም በወህኒ አንገላተው ገድለዋል። ፕሮፌሰር አስራትን ያስታውሱአል። የአሰፋ ማሩን፤ የተስፋየ ታደሰን አሙአሙአትንስ እንዴት እንረሳለን። ሌሎችንም ዳብዛቸውን ያጠፉትን የነ ወንዱ ሲራክን፤ የነ አበበ አይነኩሉን፤ የነ ፅጋየ ገ/መድህንን፤ አበራሽን እና አያሌ ታጋዮችን ጨምሮ። በምርጫ 97 ማግስትስ የነሽብሬ ደሳለኝን ገና እምቦቅቅላ ወጣት አገዳደልን እንዴት አናጣዋለን? አወ ለዚህ ደመኛ ድርጅት ከመነሻ አላማው አላማየ ብለው ስለታገሉ አባላቱ አይደለም ማውራት የፈለግሁ። ለነሱ ደጅ ጠኝወች ከጅምሩ ቆዩ ይታዩ ስለአሉት። ቆይተውም አብረው የሚቃወሙ መስለው ተቃዋሚን ስለሚያከቸለችሉት ነው ማውጋት የፈለግሁ። ሰው ሁሉ እንዲያውቃቸው የምደጋግምም ስልነዚህ አስመሳዮች ነው። ይጎዱናል ትናንትም ጎድተውናል። ዛሬም እንዲሁ እየጎዱን ነው። “ ጠላትማ ምን ጊዜም ጠላት ነው አሰቀድሞ -- አሾክሹአኪውን ነው” ይል ነበር የከፋው አንጎራጓሪ።

ቸር ይግጠመን። ሳሙኤል ሽፈራው ከ ዳላስ ቴክሳስ

EthioLion.com